# *ቅኝ አልተገዛንም የቅኝ ገዥዎች ቅርስም የለንም !!*

*ዓለማየሁ ሞገስ 11-28-17*

የኢትዮጲያ ታሪክ በተለዋዋጭ ድራማዎች ከመሞላቱም በላይ የማያባራ ሽኩቻ ሲያስተናግድ የቆየ ነው። የተፋሰሱ ሶስት ሀገሮች ሚኒስትሮች በህዳሴው ግድብ የተፅእኖ ግምገማ ወይም የውሀ ሙሊት ውይይት አለመስማማት ተከትሎ የግብፅ ሚዲያዎች ሰሙኑን ሲሰጡት የሰነበተው ሽፋን ይዘትም ወደ ኋላ ታሪካችን ጋር ተመሳሳይነት አለው። የተፈጥሮ ፀጋችንን ፍትሀዊ በሆነ መንገድ እንዳንጠቀም ለዘመናት ከተሸረበብን ሴራ ጋር ተያይዞ ሊታይ ይችላል።

ታሪካችንን ስንዳስስ የአገው ክርስቲያናዊ መንግስት ስልጣኑን ከአክሱም ዘመነ መንግስት ከተረከበ በኋላ ገጥሞት የነበረውን ፈተና ማስታዎስ ይቻላል። በ1137 የዛግዌ ስርዎ መንግስት ወደ ስልጣን ሲመጣ በሀገሪቱ ስልጣን የነበራቸውና ከግብፅ ተሹመው /ተሰይመው/ ስልጣን የያዙት ጳጳሳት ለስርዓቱ ዕውቅና አልሰጥም ማለቱን ተከትሎ የዛግዌ ንጉስ መልዕክተኛ ወደ ካይሮ በመላክ ለስልጣኑ ዕውቅና እንዲሰጣቸው እስከ መለመን መድረሳቸውን ታሪክ ይዘክረናል።

ታሪክ የሚያስረዳን በኢትዮጲያ ሀይማኖታዊ መንግስት ረጅም ጊዜ መቆየቱን ነው። ከሁሉም በላይ ደግሞ በኢትዮጲያ ለመራሄ መንግስትነት ለመብቃት ከግብፅ ኮፕቲክ ቤተ-ክርስቲያን ዕውቅና ውጭ አይታሰብም ማለት ነበር። የኢትዮጲ ህዝብ መረጠውም አልመረጠውም ለሀገራችንን የፖለቲካዊና ኢኮኖሚያዊ ዕድገት ራዕይ ኖረውም አልኖረውም መሪያችንን ግብፆች ካላመኑበትና ካልፈቀዱ ለስልጣን አይበቃም፤ በህዝባችን ዘንድም ተቀባይነት እንዳይኖረው እጅግ የተራዘመና ተለዋዋጭ ሴራ ሲሸረብ ቆይቷል ማለት ይቻላል።

ስለዚህ በግብፅ በኩል ኢትዮጲያ ላይ ስልጣን እንዲያገኝ የሚፈለገው መራሄ መንግስት ልማትን አፋጥኖ መልካም አስተዳደርን የሚያሰፍን ሳይሆን ህዝቦች እርስ በርሳቸውም ሆነ ከጎረቤቶቻቸው ጋር ሲናከሱ እንዲኖሩ የሚፈቅድ የድህነት ዘበኛ መንግስት መሆን አለበት ማለት ነው።

የሁለቱ ሀገሮች የረጅም ዘመን የግንኙነት ታሪክ የሚያስረዳው ይህንኑ ዕውነታ ነው። በግልፅ ቋንቋ ግብፅ የኢትዮጲያ ፖለቲካ ፤ኢኮኖሚና ማህበራዊ ውድቀት ባለቤት ባትሆንም ዳደ ደስታ እንዳለው በዕርግጥም ቀንደኛ ተዋናይ ነበረች ማለት ይቻላል።

ግብፅ ሲጀምር ለዚሁ ቀንደኛ የጠላትነት ተግባር በሚመስልና 5 በመቶ በማይሞሉ ኮፕክ ኦርቶዶክስ ሀይማኖት ተከታዮቿ ሳቢያ ዕምነት አይሉት መመሪያ በመላክ ቀጥሎ ልዩ ልዩ ጦርነቶችን በጎረቤተቻችንም ሆነ በውስጥ ጉዳያችን ድረስ ዘልቀው ሁከትና ብጥብጥ በመክፈትና ገንዘብ አበዳሪ ዓለማቀፍ ተቋማት ሳይቀር በምትፈጥረው አሻጥር በዓባይ ወንዝ የመጠቀም መብታችንን ለዘመናት ስትከላከል ቆይታለች።

ናስር አገራቸው ለወንዙ ምንም ዓይነት የረባ አስተዋፅኦ እንደማታበረክት እያወቁ በናይል ወንዝ የአስዋን ግድብ ሲያለሙ የላይኖቹን ተፋሰስ ሀገሮች ኢትዮጲያን ጨምሮ አላስፈቀደችም ማስፈቀድም አልነበረባትም። ሀገራችን ኢትዮጲያም ሀገሮች ለመልማት በሚያደርጉት ጥረት የራሳችንን መብትና ጥቅም እካልነካ ጊዜ ድረስ በሀገሮች መልማት ደስ የሚለን እንጅ የሚከፋን አይሆንም ።

ግብፅ በናይል ውሀ ላይ የራሷን ልማት ስታሳልጥ፤ የተፋሰሱ ሀገሮችም የሚበጃቸውን ልማት እንዳያፋጥኑ ምክንት እየሆነችና እየተከላከለች መሆን የለበትም ። ይልቁንም የተፋሰሱ ሀገሮችም በወንዙ ላይ ፍታሀዊና ዘላቂ ጥቅማቸው ሊረጋገጥ በሚችልበት መንገድ እንዲፈጠር ጥረትና ድጋፍ ማድረግ ይተበቅባታል።

ግድቡን ተከትሎም ፍትሀዊ ባልሆነ መንገድ ግብፅ የወንዙን 85% ውሀ እንድትጠቀም የ(1959) ስምምነት ተፈፅሟል። ይህ የአጠቃቀም ስምምነት እንዲቀጥልና የቅኝ ግዛት አስተሳስቦች በ21ኛ ክፍለ ዘመን ቦታ እንዲኖራቸው የሚኮረኩሩ ዘገባዎች በግብጥ ሚዲያዎች ሲቀነቀኑ ሰንብተዋል። ይህ ቅንነት የጎደለውና የዘመኑን የተፋሰሱ ህዝቦች ጥቅምም ሆነ ስነ- ልቦና ከግምት ያላስገባ ዘገባ በማነኛውም መመዘኛ ከጥቅሙ ይልቅ የግብፅን ህዝቦች ከተፋሰሱ አገሮች ጋር ያላቸውን የትብብርና ግንኙነት መንፈስ የሚጎዳ ከሁሉም በላይ ሚዲያው ሙያዊ ብቃቱን ሊያሳይ የሚችልበትን ወርቃማ ዘመን ገደል የሚጥል ነው። የግብፅ ሚዲያ የግብፅን ጥቅም የሚያስከብር ከሆነ ትክክለኛና ግልፅ መረጃ ሊያደርስ የሚችልበትን አጋጣሚ ሳይጠቀም ቀርቷል።

ግብፅ ከአባይ ውጭ ሰው ሊኖርባት የማትችል ሀገር ሆና እያለ የአባይ ፍጡር እየተባለች ትጠራለች ። በተቃራኒው ለወንዙ 86% ውሀ የምታመነጨው ኢትዮጲያ ግን በድርቅ ረሀብና ድህነት የምትቆላ ሀገር ሆና ቆይታለች።

ከውሀ ሀብታችን ብቻ 45 ሺ ሜጋ ዋት የኤሌክትሪክ ሀይል ከማመንጨት ባለፈ ለመስኖ፤ ዓሳ ዕርባታና የቱሪዝም ሀብታችንን ማሳደግ እየቻልን ለድህነትና ኋላ ቀርነት ፤ተጋልጠን እጃችንን ለምፅዋት የምንዘረጋ ከተመፅዋቾችም የመጨረሻ ተረታ ሆነን አዲሱን ሚሊነየም ተቀብለናል።

ያሳለፍነውን አንድ መቶ ሀመሳ አመታት በዓለማቀፉ ማህበረሰብ ዘንድ የነበረን የቁልቁለት ጉዞ ታሪክ በዋነኛነት የራሳችን የውስጥ ድክመት ቢኖርበትም የግብፅ ገዥ መደቦች ያራምዱት የነበረው የዜሮ ድምር ፖለቲካ የውድቀት ታሪካችን አካል ተደርጎ ሊወሰድ ይችላል።

የግብፅ ገዥ መደቦች በአባይ ወንዝ ላይ እንዳንጠቀም ሲያራምዱት የቆዩት የዜሮ ድምር ፖለቲካ ቢታወቁም አዲሱን ሚሊነዮም ስንቀበል ግን ይህን ታሪክ በሚቀይርና በተፈጥሮ ሀብታችን ከተፋሰሱ ሀገሮች ጋር የእኩልነትና የጋራ ተጠቃሚነትን የሚያረጋግጥ አጀንዳ ይዘንና ተቀብለን ነው፡፡

የውጭ ጉዳይና ብሄራዊ ደህንነት ፖሊሲያችን ከማነኛውም ሀገር ጋር የሚኖረንን ግንኙነት ኢትዮጲያ ልኡዓላሚ ሀገር መሆኗን ተቀብሎና አምኖ ነው፡፡ የኢትዮጲያ ህዝብና መንግስት ከሌላው ሀገርና ህዝብ ጋር የሚያደርገው ግንኙነትም በመከባበርና አንዱ በሌላው ሀገርና ህዝብ ጣልቃ መግባትን ይከለክላል፡፡

የኢትዮጲያ ብሄሮች ብሄረሰቦችና ህዝቦች ልዑአላዊ የስልጣን ባለቤቶች ናቸው፡፡ ግብፅ በኢትዮጲያ ህዝብ የውስጥ ጉዳይ ጣልቃ የምትገባበትን ሁኔታ ፈፅሞ የማይፈቅድ ከመሆኑም በላይ በህገ-መንግስታችን የሀገራችንን ልኡላዊነት ለድርድር እንደማያቀርብ ሁሉ ለሌሎች ሀገሮች ልኡአላዊነት ክብር ይሰጣል ፡፡

ኢትዮጲያዊያን መሪያቸውን ወደ ስልጣን የማውጣትና ከስልጣን የማውረድ ጉዳይ የራሳቸው ህገ-መንገስታዊ ስልጣን እንጅ በሀይማኖት ስም ከጎረቤት ሀገር የሚቸር ዕዳ መሆኑ ተዘግቷል፡፡ ኢትዮጲያ የህዝቦቿን ጉልበት ፤መሬት እና የተፈጥሮ ፀጋዋን አቀናጅታ ወንዞቿንም ጭምር በመጠቀም ከድህነት ለመውጣት የማንንም ፈቃድ መጠየቅ አይጠበቅባትም ፡፡ በአጭሩ ጊዜና ፍትህ ከኢትዮጲያ ብሄሮች ፤ብሄረሰቦችና ህዝቦች ጎን ቆመዋል፡፡

ልማታዊና ዲሞክራሲያዊ መስመራችን ለናይል ውሀ የረባ አስተዋፅኦ ሳታደርግ የወንዙ ዋና ተጠቃሚ የሆነችውንና የአባይ ፍጡር እየተባለች የምትታወቀው **ግብፅ ኢትዮጲ ውስጥ ልማት የማያራምድ ዘበኛ መንግስት ይኑር ከሚል የቅኝ ገዥ አስተሳሰብ** ወጥታ ለጋራና ፍታሀዊ ተጠቃሚነት ትሰለፍ፡፡ ኢትዮጲያ በቅኝ ያልተገዛች ሀገር ነች ፡፡ የቅኝ ገዥዎች አስተሳስብም በኢትዮጲያዊን ዘንድ ተፅዕኖ አልነበረውም ባይባልም አገራችንን በልማት ከመለወጥ ግን ሊያዘናጋን እንደማይችል ህዝባችን የህዳሴ ግድቡን በራሱ ወጭ መሸፈን መቻሉ የነፃነት ታሪኩም የአይበገሬነቱም ማሳያ ነው፡፡

የግብፅ ሚዲያዎች ለግብፅ ህዝብና ፖለቲከኞች የተዛባ መረጃ ከመስጠት የአዲሱን ክፍለ ዘመን የሀገሮች ክብርና ፍትሀዊ የሀብት ክፍፍል ዜማ መዘመር ይጠበቅባቸው ነበር ፡፡ የዘመናችን የጥቅም ጨዋታ ደግሞ Win -win approach እንጅ እንደ ቅን ገዥዎች the winner takes All የሚያዋጣና ተቀባይነት ያለው አይሆንም ፡፡ ስለዚህ የግብፅ ሚዲያዎች ዝማሬ በወንዛችን ላይ ከጀመርነው ባንዲራ ፕሮጀክት ሆነ ከህዳሴ ጉዞ ማደናቀፍ የሚሳካ ቁማር አይሆንም፤ አይፈቀድላትምም፡፡

የአሁኖቹ የግብፅ ገዥ መደቦች፤ ሚዲያና ሲቭል ሶሳይቲ በኢትዮጲያ ላይ ይፈፅሙት ከነበረው ታሪካዊ ዜሮ ድምር ፖለቲካ ስህተት ይልቅ ግብፅ በናይል ላይ ታራምድ የነበረው የተሳሳተ ጥቅም እንደ ሙሰቪኒ አገላልፅ ‘’ A Mother lied her baby on the street ‘’ **ህፃን ልጇን መንገድ ላይ እንደጣለች**

**እናት** ከሚያስገምታት ተግባር ወጥታ በወንዙ ላይ የትብብርና ከዚያም በኢንተቬ ስምምነት ሰነድ ላይ የፊርማ ጣቷን ለማስቀመጥ ብትጥር ከዚህ የተሻለ ጊዜ የለም ።

የውጭ ደህንነትና ብሄራዊ ፖሊሲያችን ታሪካዊ ጠላቶቻችን በውሀ ሀብታችንን እንዳንጠቀም ለዘመናት ያራምዱት የነበረውን የዜሮ ድምር ፖለቲካ የሚዘጋ የጀመርነውን ልማት የሚያፋጥን ነው።

ለአለማቀፍ ገንዘብ አበዳሪ ተቋማት እንደለመዱት ብድር እንዳያስከለክሉን ህዝባችን ግድቤን እራሴ እሰራዋለሁ፤ለብድር ከሰው ደጃፍ አልቆምም ብሎ አሁን ከ63 በመቶ በላይ አከናውኖታል። ይህ ራሱ ኢትዮጲያዊያን የነፀነትና የአኩሪ ተጋድሎ ታሪክ ማሳያ ነው ። ይህ ብቻ አይደለም ኢትዮጲያዊያን ቅኝ ገዥዎች በአፍሪካ ጥለውት የሄዱትን ጥገኛ አመለካከት የሚሰብር ፤ ቅኝ ገዥዎች ችላ ያሉት መሰረተ ልማት ደግሞ በአፍሪካ ምድር ከፍ ብሎ እንዲታይና ለአፍሪካዊያን ወገኖቻችን ትልቅ ማሳያ ለቅኝ ገዥዎችም ትምህርት የሚሰጥ ነው።

ሀገራችን ወደ ብርሀን ዘመን ለመሸጋገር የምታሳየው ፍጥነትና በአባይ ወንዝ ላይ የምንገነባው የህዳሴ ግድብ አፍሪካዊያን ሚዲያዎች የግብፅን ጨምሮ ሊደግፉትና በዓለም ሊናኙት ይገባል እንጅ አፍሪካዊ ልማትንና አፍሪካዊ ትብብር በቅኝ ግዛት ዕሳቤ ተጠልፈው ሊወናበዱ አይገባም ።